# በብልጽግና ወንጌልና በ“እምነት-ቃል” ነገረ መለኮት ላይ

## የአፍሪካ የእምነት መግለጫ

*Africa Statement on the Prosperity Gospel and Word of Faith Theology*

Copyright © 2025 by North Point Baptist Church (Kenya) is licensed under CC BY-ND 4.0. To view a copy of this license, visit https://creativecommons.org/licenses/by-nd/4.0/

Published by The Ekklesia Afrika Ltd.
P. O. Box 52861-00100
Nairobi, Kenya

Translated and published with permission.

Amharic-language edition under the title:
**በብልጽግና ወንጌልና በ“እምነት - ቃል” ነገረ መለኮት ላይ የአፍሪካ የእምነት መግለጫ**
Copyright © 2026 by Addis Baptist Church
Addis Ababa, Ethiopia

Published by Wongelu Ministries

# መቅድም

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ ብዙ አደጋዎችን ትጋፈጣለች። ከእነዚህ አንዳንዶቹ ከውጪ የሚመጡ ሲሆኑ (ሐዋርያት ሥራ 20፥29)፣ እጅግ በጣም አደገኛ የሆኑት ግን ከውስጥ የሚነሡት ናቸው (ሐዋርያት ሥራ 20፥30)። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊዎች፣ የሚያስቱ ሐሰተኛ አስተምህሮዎችንና አደገኛ የሆኑ ሐሰተኛ መምህራንን በተመለከተ ሲያስጠነቅቁ ይህን አደጋ በሚገባ አስተውለው ነበር። ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠውን የከበረውን የእምነት ሀብት ለመጠበቅ፣ ቤተ ክርስቲያን ንቁና መርማሪ እንድትሆን ጥሪ የሚያቀርቡ ሌሎች ብዙ ማስጠንቀቂያዎችም አሉ (ይሁዳ 1፥3)። ሐዋርያዊ ማስጠንቀቂያዎች፣ ሌላ ወንጌል የሚሰብኩትን "የተረገሙ" መሆናቸውን እስከማወጅ የሚደርሱ፣ እጅግ ጠንካራና የማያወላውሉ ናቸው (ገላትያ 1፥8)።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሐዋርያት ማስጠንቀቂያ እንደ ተሰጠው ሁሉ፣ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ያለችው የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንም ብዙ አስተምህሯዊ አደጋዎችን እየተጋፈጠች ነው። ንቁና ጥንቁቅ የመሆን ጥሪ ያኔ ለእነርሱ የሠራውን ያህል፣ ዛሬም ለእኛ ተግባራዊ ይሆናል። ከእነዚህ አደጋዎች መካከል ዋነኞቹ የብልጽግና ወንጌልና የእምነት - ቃል (Word of Faith) ነገረ መለኮት ናቸው። እነዚህ ትምህርቶች እርስ በርስ የሚደጋገፉ ሲሆኑ፣ የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ ከፈጸመው የቤዛነት ሥራ የተነሣ፣ በዚህ ምድራዊ ሕይወት ብልጽግናና ጤና ለክርስቲያኖች የተሰጡ በረከቶች መሆናቸውን ያስተምራሉ። እነዚህ ቁሳዊ በረከቶች የሚገኙት ደግሞ፣ እምነትን በመለማመድ ማለትም፣ ገንዘብ በመስጠትና አዎንታዊ አዋጆችን (positive confessions) በማወጅ እንደ ሆነ ይሰብካሉ።

በአፍሪካ ያሉትን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን በጥቂቱ መመልከት፣ እነዚህ አስተምህሮዎች ወደ ብዙ ጉባኤዎች ሠርገው መግባታቸውንና ተግባራዊ አስተምህሯቸው መሆኑን ይገልጣል። ጠንካራ የእምነት መግለጫና ታሪካዊ አቋም ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት እንኳ፣ በዚህ የጤናና የብልጽግና አስተምህሮ

ተወርረዋል፤ ይህም ትክክለኛውን እምነታቸውንና አቋማቸውን አዳክሟል። አንድ ጉባኤ “ፕሬስቢቴሪያን” (Presbyterian) የሚል መጠሪያ ስላለው ብቻ፣ በዌስትሚንስተር የእምነት መግለጫ (Westminster Confession) የተቀመጠውን አስተምህሮ ይደግፋል ብሎ ማመን አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል። አንድ ጉባኤ “አንግሊካን” (Anglican) የሚል መጠሪያ ስላለው ብቻ፣ ሠላሳ ዘጠኙን የእምነት አንቀጾችን ይቀበላል፣ ወይም “መጥምቃውያን” (Baptist) ስለ ተባለ ብቻ፣ የ1689ኙን የለንደን መጥምቃውያንን የእምነት አቋምን ይደግፋል ማለት አይቻልም።

ስለዚህም የብልጽግናና የእምነት ቃል ነገረ መለኮትን በሚቀበሉና በማይቀበሉ ሰዎች መካከል፣ ግልጽ የልዩነት መስመርን ለማስመር የሚረዳ መደበኛ የሆነ የእምነት አቋም ያስፈልጋል። ይህ ሰነድ፣ እኛ የምናምንባቸውንና በጥብቅ የምንከዳቸውን ጉዳዮችን የሚዘረዝር አቋም ነው። የዚህ ግብ ጤናማ ያልሆነ ክፍፍልን መፍጠር ሳይሆን፣ ይህን አደገኛ ትምህርት በተመለከተ የተለያዩ ጉባኤዎችና ቤተ እምነቶች እውነተኛ አቋማቸው ምን እንደ ሆነ ግልጽ ለማድረግ መርዳት ነው። ብዙዎች ከዚህ ሐሳብ ጋራ እንደሚስማሙና የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ከዚህ ክፉ አደጋ ለመጠበቅ እንደሚሠሩ ተስፋ እናደርጋለን።

ለሥሉስ አሐዱ አምላክ ብቻ ክብር ይሁን!

# አንቀጽ 1
# የእግዚአብሔር ሥጦታና ቁሳዊ በረከት

ሰማያዊ አባታችን መልካም እንደ ሆነና ለልጆቹም መልካም ስጦታን በመስጠት ደስ እንደሚሠኝ እናምናለን። ጤናንና ብልጽግናን ጨምሮ፣ ሁሉም መልካም ስጦታዎች ያለምንም ክፉ ሐሳብና ዐላማ ወደ እኛ የሚመጡት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ሆነ እናምናለን። እነዚህ ስጦታዎች ከእግዚአብሔር ቸርነት የተነሣ መሆናቸውን እንቀበላለን። እነዚህን ስጦታዎች የሰጠን ደስ እንድንሰኝባቸው፣ ደግሞም በትሕትናና በአክብሮት እንድንቀበላቸው ነው ብለን **እናምናለን**።

የሰማዩ አባታችን፣ አማኞች ልጆቹ በመሆናቸውና እምነት ስላላቸው ብቻ ጤና፣ ብልጽግናና ቁሳዊ በረከቶችን ሊሰጣቸው ቃል ገብቷል ብለን አናምንም። የዚህ ሕይወት ጤናና ብልጽግና የእግዚአብሔር ልጅነት ማሳያ ነው ብለንም አናምንም፤ እንዲሁም እንዲህ ያሉትን ባርኮቶች ማጣት፣ እግዚአብሔር ለምድራዊ ሕይወታችን ያለውን ዕቅድና መሻት ከማግኘት የመጐደል ምልክት ነው ብለን **አናምንም**።

(1 ሳሙኤል 2፥7፤ ማቴዎስ 7፥11፤ 1 ጢሞቴዎስ 6፥17፤ ያዕቆብ 1፥17)

# አንቀጽ 2
# የክርስቶስ የቤዛነት ሥራ አድማስ

በመስቀል ላይ የተፈጸመው የክርስቶስ ሞት፣ አሁንና ወደ ፊት ለድነታችን የሚያስፈልጉትን በረከቶች ሁሉ እንደሚያረጋግጥልን እናምናለን። የቤዛነት ዕቅዱና ንድፉ፣ በንስሓና እምነት አማካይነት ከክርስቶስ ጋራ አንድ የመሆንን፣ የመጽደቅን፣ የመቀደስንና የወደፊቱን የመክበርን ትሩፋቶች እንድናጣጥም መሆኑን እናምናለን። ስለዚህም፣ የአካላዊ ሰውነታችን መዳንና ተከትሎም የምንቀበለው ፍጹም ጤንነትና ብልጽግና፣ በክብር የሚመጣው የድነታችን አካል ነው ብለን **እናምናለን።**

በመስቀል ላይ የተፈጸመው የክርስቶስ የቤዛነት *ሥራ፣* በምድር ላይ እያለን የጤናና የብልጽግና ባርኮቶችን ያለመቋረጥ የማግኘት ዋስትና ይሰጠናል ብለን አናምንም። በተጨማሪም፣ በመስቀል ላይ የተገኘውን ሙሉ ድነት፣ በአሁኑ ሕይወትና በሚመጣው የክብር ዘመን መካከል ልዩነት በሌለው ሁኔታ፣ ቅዱሳን በዚህ ምድራዊ ሕይወት ፍጹም በሆነ መልኩ ያጣጥሙታል ብለን **አናምንም።**

(*ሮሜ* 4፥25፤ 8፥23፤ 2 *ቆሮንቶስ* 5፥21፤ *ኤፌሶን* 1፥1-11፤ *ቲቶ* 2፥11-14፤ *ዕብራውያን* 10፥14፤ 1 *ጴጥሮስ* 2፥24-25፤ *ራእይ* 21፥1-7)

# አንቀጽ 3
# የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ (ሥነ-አፈታት)

በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በየትኛውም ውስን ምንባብ ውስጥ ታስቦ የተቀመጠውን የመንፈስ ቅዱስን ትርጒም፣ የምንባቡን የሥነ ጽሑፍ ዘውግ ግምት ውስጥ በማስገባትና መደበኛውን የሰዋሰው መርሖችን በመከተል፣ በእውነት ማወቅ እንደሚቻል እናምናለን። በተጨማሪም የየትኛውም ምንባብ ትርጒም፣ ከተቀመጠበት ሥነ ጽሑፋዊ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ነገረ መለኮታዊ ዐውዶች ጋራ የሚስማማ እንደ ሆነ እናምናለን። እንዲሁም ደግሞ፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ትክክለኛ ትርጓሜ፣ ጠቅለል ባለ መልኩ በታሪክ ውስጥ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍቱን ከተረዳችበት መንገድ ጋራ የሚስማማ መሆን እንዳለበት **እናምናለን።**

ቅዱሳት መጻሕፍት፣ በአንጻራዊ ምልከታ ወይም ቀጥተኛ በሆነ የምስጠራ (allegories) አተረጓጐም ላይ ተመሥርቶ በዘፈቀደ ይተረጐማሉ ብለን አናምንም። "የተቀቡ" ሰዎች ብቻ ሊያውቋቸውና ሊያስተምሯቸው የሚችሏቸው ስውር መገለጦች በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አሉ ብለን አናምንም። የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጒም ለመረዳት አእምሯችንን (ዕውቀታችንን) መጠቀማችን፣ በአብርሆት ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ይቃረናል ብለን **አናምንም።**

(ሉቃስ 24፥26-27፤ 44-47፤ ዮሐንስ 5፥39-40፤ ሮሜ 15፥4፤ 2 ጢሞቴዎስ 3፥16-17፤ 2 ጴጥሮስ 1፥20-21፤ 3፥16-17)

# አንቀጽ 4
# ብሉይ ኪዳንና ቁሳዊ በረከቶች

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋራ የገባው ኪዳን፣ በቤዛነት ታሪክ ውስጥ ከእነርሱ ጋራ የነበረው እውነተኛ ግንኙነት ነጸብራቅ መሆኑን እናምናለን። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን፣ ለእነርሱ ያለው መልካምነትና ፍቅር ማሳያ አድርጎ፣ ቁሳዊ ብልጽግናን ለእስራኤል ሕዝብ ተስፋ አድርጎ መስጠቱን እንቀበላለን። ምንም እንኳ እስራኤል በዘዳግም 28 እና በመሳሰሉት ምንባባት የተገለጹትን ቁሳዊ በረከቶች በቋሚነት ባታስጠብቅም፣ የብሉይ ኪዳን ሕጎችን በመጠበቅ፣ የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር የመጠየቅ መብት እንደ ነበራቸው **እናምናለን**።

ክርስቲያኖች አሁን ከእግዚአብሔር ጋራ ያላቸው ግንኙነት፣ እስራኤል በቀደመው ኪዳን ሥር ከነበራትን ግንኙነት ጋራ ተመሳሳይ አይደለም ብለን እናምናለን። ስለዚህም ዛሬ ላይ ያሉ ክርስቲያኖች፣ ለጥንቷ እስራኤል በብሉይ ኪዳን ተስፋ የተገባውን ቁሳዊ በረከት እንደ መብት የመጠየቅ ሥልጣን አላቸው ብለን **አናምንም**።

(*ዘፍጥረት* 12፥2-3፤ *ዘፀአት* 19፥4-6፤ *ዘሌዋውያን* 26፥3-13፤
*ዘዳግም* 7፥13-14፤ 28፥1-2፤ *ሚልክያስ* 3፥10-12)

# አንቀጽ 5
# የትውልድ ርግማንና የነጻ መውጣት አገልግሎት

በእግዚአብሔር የቀደመው ኪዳን ሥርዐት ውስጥ፣ እስራኤላውያን የኪዳኑን ግዴታዎችን በከፋ ሁኔታ በማፍረሳቸው ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች መሆናቸውን እናምናለን። እነዚህ ኪዳንን የማፍረስ መዘዞች፣ አንዳንድ ጊዜ የወደ ፊቱንም ትውልድ ሊጐዱ ይችላሉ ብለን እንቀበላለን። በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር በደላቸውን የሚያውቅ አምላክ ስለ ሆነ፣ እስከ አራተኛው ትውልድ ድረስ ፍርድን ማምጣት መብቱ እንደ ሆነ እናምናለን። ይህም እውነታ ክርስቶስ በሕዝቡ ፈንታ ርግማን ሆኖ በሞተ ጊዜ ማብቃቱን **እናምናለን**።

ዛሬ ላይ ክርስቲያኖች፣ ከገዛ ራሳቸው የቀረ ኀጢአት፣ ወይም ካላመኑ የቀደሙ አባቶቻቸው የተነሣ "የትውልድ ርግማን" (generational curse) ወይም ሌላ ዐይነት ርግማን ሥር ሊወድቁ ይችላሉ የሚለውን ሐሳብ አጥብቀን እንቃወማለን። ክርስቲያኖች ያለፈውን የትውልድ ሐረጋቸውን በመመርመር፣ በክርስቶስ ከተገኘው ፍጹም ድነት ውጪ፣ "የዘር እስራት" ከሚሉት ርግማን ልዩ የሆነ ነጻ መውጣትን (deliverance) መፈለግ አለባቸው ብለን አናምንም። በተጨማሪም፣ እነዚህ ነጻ መውጣቶች ልዩ የጸሎት ቦታዎችን በመጐብኘት፣ "ልዩ ቅባት" ባላቸው ሰዎች እጅ በማስጫን፣ ወይም ገንዘብን በመስጠት ይገኛሉ ብለን **አናምንም**።

(*ዘፀአት* 20፥5፤ *ዘሌዋውያን* 26፥14-39፤ *ዘዳግም* 11፥26-28፤ 30፥15-20፤ *ኤርምያስ* 32፥18-19፤ *ገላትያ* 3፥13)

# አንቀጽ 6
# መሠዊያዎች፣ መቅደሶችና መንፈሳዊ ስፍራዎች

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ራሱን ለሰዎች የገለጠው በጊዜያዊ መሠዊያዎች፣ ማደሪያ ድንኳኖችና መቅደሶች ውስጥ መሆኑን እናምናለን። እነዚህ ቦታዎች እግዚአብሔርና ሰው በምድር ላይ የሚገናኙበትን ሥፍራዎች ይጠቁማሉ። ስለዚህም እነዚህ መሠዊያዎች፣ ማደሪያ ድንኳኖችና መቅደሶች በእግዚአብሔር ሕዝብ አምልኮ ውስጥ በትክክል አስፈላጊነት ነበራቸው። በአሁኑም ጊዜ፣ እነዚህ ማደሪያዎች የእግዚአብሔር መገለጥ ፍጻሜ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጻሜያቸውን ማግኘታቸውን እናምናለን። እርሱ ሰውና መለኮት የሚገናኙበት ፍጹሙ ማረፊያ ነው። ከኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ የትኛውም ምድራዊ ስፍራ ወይም ሕንጻ፣ መለኮታዊ ባርኮቶችን ለማግኘት የተለየ መንፈሳዊ ጠቀሜታ እንደሌለው **እናምናለን**።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች ከሰማይ ጋራ የሚያገናኙ መሠዊያዎች ሊኖራቸው ይገባል ብለን አናምንም። በተጨማሪም ክርስቲያኖች፣ መንፈሳዊ ይዞታን ለመቈጣጠር የሚታዩና የማይታዩ መሠዊያዎችን መሥራት አለባቸው የሚለውን ዕሳቤ አንቀበልም። የማይታዩ መሠዊያዎችን ለማፍረስ እንዲሁም ሰዎችን፣ ኢብያተ ክርስቲያናትን ወይም ከተማዎችን ከክፉ መናፍስት ለማስለቀቅ ልዩ የሆነ “ነጻ መውጣት” አስፈላጊ ነው ብለን **አናምንም**።

(*ዘፍጥረት* 13፥4፤ *ዘፀአት* 25፥8-9፤ *ዮሐንስ* 2፥19-22፤ 4፥21-23፤ *ዕብራውያን* 8፥1-2፤ 9፥11-12፣ 24፤ 10፥19-22)

# አንቀጽ 7
# መከራና የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት

በዚህ የወደቀው ዓለም ውስጥ፣ በተለያየ መልኩ የሚመጣ መከራ የተለመደ መሆኑን እናምናለን። እንዲሁም፣ እግዚአብሔር ከራሱ መልካም፣ የፍቅርና የጥበብ ዐላማዎች የተነሣ በአዎንታዊ መልኩ መከራን በሕዝቡ ላይ እንዲመጣ የሚወስን አምላክ መሆኑን እናምናለን። መከራ በክርስቲያኖች ዘንድ እንደ እንግዳ ነገር ተደርጎ ሊቆጠር አይገባም። ነገር ግን በሚመጣው የክብር ዘመን፣ የመከራ መወገድና መጥፋት የክርስቲያን ተስፋ አካል መሆኑን እንቀበላለን። ክርስቲያኖች፣ መከራን በመከራነቱ መፈለግና መናፈቅ አይገባቸውም፤ ሆኖም ግን መከራን በትዕግስትና በጽናት የሚቀበሉና በመከራቸውም ውስጥ ደስተኞች መሆን እንደሚገባቸው **እናምናለን።**

መከራ ወደ ሕይወታችን የሚመጣው የግድ ከእምነታችን መድከም የተነሣ ነው የሚለውን አመለካከት አጥብቀን እንቃወማለን። መከራ የሚከሠተው እግዚአብሔር ለሕይወታችን ካለው ፈቃድ ውጭ (በተቃርኖ) ነው የሚለውን ሐሳብ አንቀበልም። በተጨማሪም፣ የመከራ በሕይወታችን መከሠት "ለእግዚአብሔር ሰዎች" ገንዘብን በመስጠት፣ አዎንታዊ ዐዋጆችን በማወጅ፣ ወይም ትንቢታዊ ንግግሮችን በማድረግ የሚፈታ ልዩ የሆነ "ነጻ መውጣት" ያስፈልገዋል ብለን **እናምንም።**

(ዮሐንስ 16፥33፤ ሐዋርያት ሥራ 14፥22፤ ሮሜ 5፥3-5፤ 8፥17-19፤ 2 ቆሮንቶስ 1፥3-5፤ ፊልጵስዩስ 1፥29፤ 3፥10፤ 2 ጢሞቴዎስ 3፥12፤ ያዕቆብ 1፥2፤ 1 ጴጥሮስ 4፥12-19)

# አንቀጽ 8
# ገንዘብና በረከት

ለኢጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ገንዘብን ጨምሮ የኛ የሆነውን ሁሉ መስጠት እጅግ ጠቃሚ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተግባር ነው ብለን እናምናለን። ክርስቲያኖች ገንዘባቸውን ሲሰጡ በልግስና፣ አዘውትረውና በመሥዋዕትነት እንዲሰጡ በእግዚአብሔር የተጠሩ መሆናቸውንም እናምናለን። ይህን በማድረግ ሀብታቸውን ብልና ዝገት በማይደርስበት፣ ሌቦች ሰብረው ሊሰርቁት በማይችሉበት በሰማይ እያከማቹ መሆኑን እናምናለን። ከዚህም በላይ፣ ከመቀበል ይልቅ መስጠት፣ የበለጠ መባረክ መሆኑንና በመስጠት ዕድል ውስጥ ፍሬያማነትና በረከት ከእግዚአብሔር እንደሚመጡ **እናምናለን**።

ገንዘባችንን መሥጠት ጤናና ብልጽግና፣ እንዲሁም ሌሎች ምድራዊ በረከቶችን ለማግኘት በእግዚአብሔር የታቀደ መንገድ መሆኑን አንቀበልም። ክርስቲያኖች ተአምራትን ከእግዚአብሔር መግዛት እንደሚችሉ፣ ወይም እግዚአብሔር ገንዘብን ከማይሰጡ ሰዎች ጸጋውን እንደሚከለክል የሚያስተምሩ ትምህርቶችን ሁሉ እንቃወማለን። ደግሞም አንድ ሰው ከገቢው ዐሥራትን ባለ መስጠቱ፣ ባልተጠበቁ ዕዳዎች፣ በሕመሞችና በኪሣራዎች ወይም እንዲህ በመሳሰሉ ቅጣቶች የእግዚአብሔር ርግማን ይወርድበታል ብለን በፍጹም **እናምንም**።

(*ሐዋርያት ሥራ* 20፥35፤ 2 *ቆሮንቶስ* 8፥1-5፤ 9፥6-11፤ *ኤፌሶን* 4፥28፤
1 *ጢሞቴዎስ* 6፥6-10፣ 17-19፤ *ዕብራውያን* 13፥16)

# አንቀጽ 9
# የቃላት ኀይልና የአንደበት አጠቃቀም

ንግግራችን (ቃላቶቻችን) በሌሎች ላይ አስከፊ ጉዳትን ሊያደርሱ ወይም ሌሎችን ሊረዱ እንደሚችሉ እናምናለን። የዚህም እንድምታው (ምሳሌያዊ በሆነ አነጋገር)፣ ሕይወትና ሞት በአንደበት ኀይል ውስጥ መሆናቸውን እናምናለን። በርግጥም ቃላት በሰዎች ስሜትና ግንኙነት ላይ ተጽእኖ የማድረግ ኀይል አላቸው። ስለዚህም ክርስቲያኖች እውነትንና ሌሎችን የሚያንጸውን ብቻ በመናገር፣ አንደበታቸውን በጥበብ መጠቀም አለባቸው ብለን እናምናለን። በተጨማሪም፣ ሌሎችን ለማነጽና ለመርዳት ስንናገር፣ ዐላማዎቹን በቃሉ አማካይነት የሚፈጽመውን እግዚአብሔርን እየመሰልንና እያንጸባረቅን ነው ብለን **እናምናለን**።

የሰዎች ቃላትና ንግግሮች፣ የእግዚአብሔር ቃል ያለውን ዐይነት የመፍጠር ኀይል አላቸው ብለን በፍጹም አናምንም። ክርስቲያኖች አዎንታዊ ቃላትን በመናገር ነገሮችን ወደ ህልውና ማምጣት ይችላሉ የሚለውን ሐሳብ አንቀበልም። መታመምን ወይም ማጣትን በግልጽ መናገር እነዚህን እውነታዎች ስቦ ያመጣቸዋል ወይም በቋሚነት እንዲቀጥሉ ያደርጋቸዋል ብለን **አናምንም**።

(ምሳሌ 18፥21፤ ማቴዎስ 12፥36-37፤ ኤፌሶን 4፥25-29፤
ቈላስይስ 4፥6፤ ያዕቆብ 1፥19፤ 3፥1-12)

# አንቀጽ 10
# በእግዚአብሔር መልክ መፈጠር

ሁሉም ወንዶችና ሴቶች በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥረዋል መፈጠራቸውንና ይህም ታላቅ ክብርን እንደሚሰጣቸው፣ ከተቀረው ፍጥረትም እንደሚለያቸው እናምናለን። በተጨማሪም፣ ሰዎች በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠራቸው፣ በአካላዊና አእምሯዊ ጥረቶች አማካይነት ጥሬ ዕቃዎችን ወደ ጠቃሚ ምርቶች በመለወጥ (በማልማት) ከእግዚአብሔር ጋራ በትብብር የሚሠሩ መጋቢዎች ሊሆኑ ይችላሉ ብለን **እናምናለን።**

ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር መልክ መፈጠራቸው፣ ልእለ ተፈጥሯዊ ሥልጣን ያላቸውና በቃላቸው የሌሉ ነገሮችን ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣት የሚችሉ "ትናንሽ አማልክት (little gods)" ያደርጋቸዋል ብለን በፍጹም አናምንም። መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ መሪዎችንና ፈራጆችን "አማልክት" ብሎ ሲጠራ፣ መለኮታዊ አካላት ናቸው ብሎ እየተናገረ ነው የሚለውን መረዳት አንቀበልም። በእግዚአብሔር መልክ መፈጠር ማለት፣ ከሰዎችና ከእንስሳት መራባት ጋራ በሚመሳሰል መልኩ፣ እግዚአብሔር ራሱን በእነርሱ ውስጥ ማራባቱ እንደ ሆነ **አናምንም።**

(*ዘፍጥረት* 1፥26-28፤ 2፥19፤ *ኢዮብ* 38፥1-42፥6፤ *መዝሙር* 82፥6-7፤ *ሐዋርያት ሥራ* 20፥35፤ 2 *ተሰሎንቄ* 3፥10-12)

# አንቀጽ 11
# የእምነት ምንነት

እምነት ማለት በእግዚአብሔርና በተገለጡት ተስፋዎቹ ላይ የምንታመንበት የርሱ የጸጋ ስጦታ መሆኑን እናምናለን። እምነት ለድነት እጅግ አስፈላጊ እንደ ሆነና የእግዚአብሔርን የማዳን ጸጋ እጃችንን ከፍተን የምንቀበልበት መሣሪያ መሆኑን እናምናለን። ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት የማይቻል መሆኑንና የክርስቲያን ሕይወት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በእምነት ሊኖር የተገባው መሆኑንም እናምናለን። ደግሞም እግዚአብሔር በእምነት ደስ የሚሰኝ መሆኑንና ልጆቹ ሲጸልዩና በእምነት ሲኖሩ፣ እንደ ፈቃዱ አዎንታዊ ምላሽ እንደሚሰጥ **እናምናለን።**

እምነት፣ ክርስቲያኖች የሚፈልጉትን ነገር ወደ ህልውና ለማምጣት የሚጠቀሙበት ግላዊ ኀይል እንደ ሆነ በፍጹም አናምንም። እምነት፣ በራሱ የመፍጠር ኀይል ያለው እግዚአብሔር ራሱ የሚገዛለት ራሱን የቻለ ሕግ ነው የሚለውን ትምህርት አጥብቀን እንቃወማለን። በተጨማሪም፣ እምነት ከመከራና ከሕመም ይከልለናል ብለንም **አናምንም።**

(ኤፌሶን 2፥8-9፤ ፊልጵስዩስ 1፥29፤ 2 ጴጥሮስ 1፥1፤
ዕብራውያን 11፥6፣ 13)

# አንቀጽ 12
# ክርስቲያናዊ አእምሮ

የክርስቲያኖች አእምሯዊና ስሜታዊ ሕይወት ለአጠቃላዩ መንፈሳዊ ጤንነታቸው በጣም አስፈላጊ ነው ብለን እናምናለን። የክርስቲያኖች አስተሳሰብ፣ አኗኗራቸውንና ቅድስናቸውን ይወስናል ብለን እናምናለን። ስለዚህም ክርስቲያኖች፣ በቋሚነት የእግዚአብሔርን ቃል በመማርና በማሰላሰል አእምሯቸውን የማደስ ግዴታ እንዳለባቸው **እናምናለን።**

አዎንታዊ የሆኑ ነገሮችን በአእምሮ ማሰብና ምስል መከሠት፣ እነዚህን ነገሮች ወደ ቁሳዊው ዓለም የመሳብ ኀይል አላቸው ብለን አናምንም። እነዚህ በምናብ የመመልከትና የማሰብ ዘዴዎች፣ እግዚአብሔር ጤናና ብልጽግናን እንዲያመጡ ከወሰናቸው መንገዶች መካከል ናቸው ብለን ፈጽሞ **አናምንም።**

(ሮሜ 12፥1-2፤ ኤፌሶን 4፥17-24፤ ፊልጵስዩስ 2፥5-11፤
ቈላስይስ 3፥12-17፤ 2 ጴጥሮስ 1፥3)

# አንቀጽ 13
# የሽማግሌዎችና የመጋቢዎች ኀላፊነት

እግዚአብሔር፣ በጉባኤዎች ላይ እረኞችና የበላይ ጠባቂዎች ሆነው እንዲያገለግሉ፣ ሽማግሌዎችን ሾሟል ብለን እናምናለን። ይህም ዕድልና ታላቅ ኀላፊነት መሆኑን እናምናለን። በታማኝ እረኞች ትምህርትና ጥበቃ ሥር፣ ጉባኤዎች በመንፈሳዊ አቅጣጫ እንዲለመልሙና በዚህ ምድር በሚያደርጉት የመናኝነት ጉዞ የተጠበቁ እንዲሆኑ የእግዚአብሔር ሐሳብ መሆኑን እናምናለን። ስለዚህም ሽማግሌዎች፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋራ በተስማማ መልኩ፣ መንጎቻቸውን የመምከርና የመንከባከብ የውክልና ሥልጣን ያላቸው መሆኑን **እናምናለን።**

የትኛውም መጋቢ የየትኛውንም ክርስቲያን መንፈሳዊ ዕጣ ፈንታን ይቈጣጠራል ብለን አናምንም። አንድ ክርስቲያን በእምነቱ ያለውን ዕድገትና መንፈሳዊ ደስታ ከአንድ መንፈሳዊ መሪ ጋራ የተሳሰረ ነው የሚለውን ትምህርት እንቃወማለን። በተጨማሪም ክርስቲያኖች ለመጋቢዎቻቸው ፍጹም የሆነ ታማኝነት፣ ፍርሃትና አክብሮትን መስጠት አለባቸው፣ አለዚያ የእግዚአብሔርን ርግማን ይቀበላሉ ብለን በፍጹም **አናምንም።**

(ሐዋርያት ሥራ 14፥23፤ 20፥28፤ ኤፌሶን 4፥7-12፤ ቲቶ 1፥5፤
ዕብራውያን 13፥17፤ 1 ጴጥሮስ 5፥1-4)

# አንቀጽ 14
# የሰው ልጅ ዋነኛ ዐላማ

እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪነቱ ሰውን ለምን እንደ ፈጠረውና ሰውስ ምን መሻት እንዳለበት በግልጽ እንደ ተናገረ እናምናለን። ይህም የሰው ልጅ ዋነኛ ዐላማ፣ እግዚአብሔርን ማክበርና ለዘላለም በርሱ ደስ መሰኘት ነው። ስለዚህም ሰው፣ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ ይልቅ፣ እግዚአብሔርን የከበረ ሀብቱ አድርጎ ሲቈጥር፣ በእግዚአብሔር ከተፈጠረበት ዐላማ ጋራ በእጅጉ ይስማማል ብለን እናምናለን። በውድቀት ምክንያት ግን የሰው ዘር መሻትና ፍላጎት ተዛብቷል፤ ይህም መልካም ስጦታዎችን ከሰጪው ይልቅ፣ የተፈጠሩ ነገሮችንም ከፈጣሪው ይልቅ እንድንፈልግ አድርጎናል ብለን **እናምናለን።**

የእግዚአብሔርን ቃል መለኪያ ሳያደርግ፣ የሥጋዊ ዐይን ምዘና (ፍርድ) መልካም የሆነውን ነገር በትክክል ሊረዳ ይችላል ብለን አናምንም። ሰዎችን ለማነሣሣት በማሰብ ኀጢአተኛና የተዛባ ምኞታቸውን ማባበልና መማረክ ማናቸውንም መልካም ፍሬ ሊያፈራ ይችላል ብለንም አንቀበልም። እንዲሁም ጤናንና ብልጽግናን ጨምሮ፣ እግዚአብሔር ለየትኛውም ግብ ማሳኪያ ወይም መወጣጫ መንገድ ሆኖ ሊያገለግል ይገባል የሚለውን አመለካከት በፍጹም **አናምንም።**

(ዘፍጥረት 1፥1፤ 2፥16-17፤ ዘፀአት 20፥2-4፤ ኢሳይያስ 43፥6-7፤ ሮሜ 1፥25፤ 1 ቆሮንቶስ 10፥31፤ ኤፌሶን 2፥1-10)

# Initial Signers

Allan Waruhiu
*Pastor, Mercy Nairobi Church, Kenya*

Arphaxad Chege
*Pastor, Presbyterian Church of East Africa, Kenya*

Benard Kariuki Mbugua
*Pastor, GracePoint Church Thika Road, Kenya*

Bernard Kuria
*Pastor, Trinity Baptist Church Kasarani, Kenya*

Charles Maina Njau
*Pastor, Buruburu Baptist Church, Kenya*

Chopo Mwanza
*Pastor, Faith Baptist Church Riverside, Zambia*

Chris Kiagiri
*Pastor, North Point Baptist Church, Kenya*

Confex Makhalira
*Pastor, Christ Presbyterian Church, Malawi*

Dan Gachuki
*Pastor, Emmanuel Baptist Church, Kenya*

Daniel Mutuku
*Elder, Buruburu Baptist Church, Kenya*

Danson Ottawa
*National Director, Africa Centre for Apologetics Research (ACFAR), Kenya*

Dieudonné Tamfu
*Pastor, Église Baptiste Bethléem, Yaoundé, Cameroon*

Dominic Kabaria
*Pastor, Trinity Baptist Church, Kenya*

Emmanuel Kwasi Amoafo
*Clergy, Anglican Church of Kenya, Kenya*

Fidel Nyikuri
*Lead Pastor, GracePoint Church Limuru, Kenya*

Graham Heslop
*Editor in Chief, TGC Africa, South Africa*

Harrison Mungai
*Lead Pastor, GracePoint Church Kikuyu, Kenya*

Isaiah Maina
*Pastor, Trinity Baptist Church Kasarani, Kenya*

Joe Mwita Thwagi
*Pastor, Upendo Gospel Community Church, Kenya*

John Musyimi
*Lead Pastor, North Point Baptist Church, Kenya*

Joseph Masunga
*Pastor, Injili Bible Church, Kenya*

Joshua Lemayian
*Associate Pastor, Emmanuel Baptist Church, Kenya*

Ken Mbugua
*Lead Pastor, Emmanuel Baptist Church, Kenya*

Kevin Nyagaka
*Pastor, Upendo Gospel Community Church, Kenya*

Kyle Tamblyn
*Youth Pastor, Honeyridge Baptist Church, South Africa*

Mark Ben Thuku
*Pastoral Resident, North Point Baptist Church, Kenya*

Matt Elmore
*Director, Kuza, Kenya*

Mpumelelo Kunene
*Pastor, Heritage Baptist Church, South Africa*

Peter Kamau
*Pastor, GracePoint Church Waiyaki Way, Kenya*

Philip Ipala
*Pastor, Cornerstone Baptist Church, Nairobi, Kenya*

Philip S. Hunt
*Pastor, Kitwe Church, Zambia*

Raymond Ndung'u
*Teaching Assistant, Nairobi Institute of Reformed Theology, Kenya*

Rodgers Atwebembeire
*Regional Director, Eastern Africa, Africa Centre for Apologetics Research (ACFAR), Uganda*

Samuel O. Oluoch
*Pastor, Grace Baptist Church, Nairobi, Kenya*

Selian Meoki
*Executive Director, Ekklesia Afrika, Kenya*

Seth Diang'a
*Pastor, Redeemer Bible Church, Kenya*

Titus Mburu
*Elder, GracePoint Church Kikuyu, Kenya*

Tommie van der Walt
*Executive Director of Imprint; Elder, Brackenhurst Baptist Church, South Africa*

# What You Can Do

1. Sign the statement online at *www.africastatement.org/sign*

2. Share the online version of the statement with others on social media: *www.africastatement.org*

3. Point others to sound resources on the prosperity gospel, such as the ones featured under *Recommended Resources.*

4. Consider using this statement to vet potential partners for your church, seminary, or ministry.

# Recommended Resources


John Musyimi
*A Counterfeit Gospel: Discerning the Poverty of the Prosperity Gospel*
Nairobi: Ekklesia Afrika, 2019
www.ekklesiaafrika.org

Ken Mbugua et al.
*Prosperity? Seeking the True Gospel*
Nairobi: ACTS/TGC, 2015
www.actskenya.org

Emmanuel Kwasi Amoafo
*Stand Up for the Gospel: Getting the Church Back on Track*
Oasis International, 2022
www.oasisinternationalpublishing.com

WONGELU MINISTRIES

Healthy Churches for the glory of Christ

ጤናማ

አብያተክርስቲያናት

ለክርስቶስ ክብር